FROM OBLIVION TO MEMORY

# The FOM Newsletter

*Commemorating Ethiopian prisoners of the Italo-Ethiopian War*

VOL. 1 · NO. 1 | JUNE / JULY 2026 | fromobliviontomemory.org

## ከዝግጅት ክፍላችን

እንኳን ወደ መጀመሪያ እትማችን በደህና መጣችሁ!

እኛ በፋሺስት ኢጣልያ ጨካኝ የወረራ ዘመን ከአገራቸው ተግዘው በኢጣልያና በሌሎች አገሮች ታስረው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ተወላጆች ስንሆን የእስረኞቹ ታሪክ ደብዝዞ እየጠፋ መሆኑን በመገንዘብና የደረሰባቸውን እንግልትና የከፈሉትን መስዋዕትነት መዘከር ግዴታ መሆኑን በመረዳት በመተባበር ማሕበር አቋቁመናል።

ይህም ዕድል የተፈጠረው የኛው ዘመዶች ታስረው የነበረበትን አዚናራ ደሴትን ለመጎብኘት በነሐሴ 2017 የተወሰንን የቤተሰብ አባላት ወደዚያው ባቀናንበት ወቅት ነበር። እስር ቤቱን ስንጎበኝ፣ ካላ ሬያሌ በሚገኘው ሆስፒታል ሕንፃ ውስጥ ግርግዳው ላይ የአንዲት ኢትዮጵያዊት ሴት፣ ከአንድ ትንሽ ወንድና አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ ጋር የተነሳችው ትልቅ ፎቶግራፍ ተሰቅሎ አየን። ከዚያን ዘመን እስረኞች መካከል ዛሬ በሕይወት ያሉት ያቺ በፎቶግራፉ ላይ የምትገኘው ትንሺ ልጅ፣ የዛሬይቱ የ94 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ብቻ ናቸው።

ይህ ከብዙ አሥርት ዓመታት በኋላ የተደረገ ጉዞ ይህን ታሪክ ሰብስቦ ማቆየት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እጅግ አመላካች የሆነ አጋጣሚ ነበር። ለዚህም ነው ወደየመጣንበት ከተመለስን በኋላ ድርጅት አቋቁመን ይህን ዓላማ ለማሳካት ጥናት ማካሄድ፣ ወገን ማነቃቃትና መደራጀት የጀመርነው። ይህም የመጀመሪያው እትማችን ለዚህ ሁሉ ዘመናት ድምፃቸው ያልተሰማላቸው ወገኖቻችንን ታሪክ ለመንገር ያለንን ቁርጠኝነት ያሳያል።

እኛም በየግዜው ከሌሎች እስረኞች ተወላጆች ጋር በያሉበት ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ለመመሥረት እንጥራለን። ይህ ታሪክ ከኛ ጋር የሚያስተሳስራችሁ፣ እንዲሁም ታሪኩና ዓላማው የሚማርካችሁ ሁሉ አብራችሁን እንድትጓዙም እንጋብዛለን። በሕይወት ጉዞ ውስጥ የዚህን ታሪክ ትውስታን ለማጎልበት፣ በማንኛውም ረገድ የምታደርጉት ትብብር ለታለመው እቅድ ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

አብረን ሆነን ያለፈውን በማስታወስ ለወደፊቱ ትውልድ የሚሆን ቅርስ እንገነባለን። በዚህ በመጀመሪያው ቅፅ በዚያን ዘመን እስረኛ የነበሩ ሁለት ሰዎች ታሪክ ቀርቧል፣ እንዲሁም አንድ ታሪካዊ ክስተት ተዘግቦ ለንባብ ቀርቧል። በቀጣይ እትሞቻችንም፣ የተለያዩ ሰዎች የሕይወት ታሪክ መዘከሩን እንቀጥላለን።

## ተለይተው የቀረቡ ጽሑፎች



ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት

### ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት በ19 ዓመት ዕድሜአቸው ከፈረንሣይ አገር ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጣልያን አስሮ፣ ከአገራቸው አውጥቶ ከሦስት መቶ በላይ ከሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር አዚናራ ወስደው አስረዋቸው ከዚያ ደግሞ ወደ ሎንጎቡኮ አዛውረዋቸዋል።

የደጃዝማች ግርማቸው የሕይወት ጉዞ የትጋት፣ የፅናትና የሕዝብ አገልግሎት ታሪክን ያካተተ ነው። ከእስር ከተፈቱ በኋላ የተዋጣላቸው ጸሐፊ ተውኔትና ደራሲ ሆነዋል።

ከዚህም መሃል እንደ እስረኛ በልጅነት የኖሩበትን ሎንጎቡኮን በሮም የኢትዮጵያ አምባሳደር በነበሩበት ጊዜ እንደነፃ ሰው ቤተ ሰባቸውን አስከትለው ለመጎብኘት የሚገርም ዕድልን ያገኙ ሰው ናቸው።

ከአዚናራ እስረኞች መካከል ታሪካቸው በደንብ ተዘግቦ ከተቀመጠው ጥቂት ሰዎች መካከል አንዱ ደጃዝማች ግርማቸው አንዱ ናቸው። ይህም በቅርቡ ለኅትመት በቅቶ ለንባብ ይቀርባል።

ይቀጥላል...

### ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ

ተግዳሮትና ፈተናን ተቋቁመው ረዥም ዕድሜ ኖረው በዘጠናዎቹ ዕድሜ ክልል ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ ገና ወጣት ሆነው የጥቁር አንበሳ መሥራች አባል ነበሩ። ከዚያም ጣልያኖች ይዘው በእስረኝነት ወደ አዚናራ ከወሰዷቸው በኋላ ለሌሎች እስረኞች ከለላና ድጋፍ በመሆን ይታወቃሉ። ወይዘሮ ስንዱ መምህርት፣ ደራሲ፣ የሴቶች መብት ተሟጋች፣ ፖሊቲከኛና የሌላም ብዙ ሙያ ባለቤት ነበሩ።

ይቀጥላል...



ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ



ጥቁር አንበሳ ከሚባሉ ጋር የሚያያዙ አባላት

### ጥቁር አንበሳ

ይህ አጠር ያለ ፅሑፍ ስለ ጥቁር አንበሳ ያትታል። ጥቁር አንበሳ ፋሽዝምን ለመታገል በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተደራጀ የመጀመሪያው ቡድን ነው።

ጥቁር አንበሳ የተቋቋመው ኢትዮጵያ ውስጥ በኢጣልያ ወረራ ግዜ ሲሆን፣ የሥነምግባር፣ የአገር ኩራትና የብርታት ተምሳሌት የሆነ ኃይል ነበር። ቡድኑ ዕድሜው አጭር ቢሆንምና አባላቱ ብዙ ባይሆኑም እንኳ፣ ቅኝ ገዥዎችንና ጭቆናን ለመገዳደር ያደረጉት ተጋድሎ በኢትዮጵያም ለቀጣዩ ትውልድ፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ መድረክ ለሌሎች ታጋዮች አስተማሪ ለመሆን በቅቷል። የጥቁር አንበሳ ታሪክ እነሆ።

ይቀጥላል...

# ሰሞነኛ ሁነቶች

## የ AAIS ስብሰባ

በመጭው የኢጣልያ ጥናት በአሜሪካ ማሕበር ስብሰባ ላይ ተገኝተን ድርጅታችንን ለማስተዋወቅ ባገኘነው ዕድል መሠረት ይህንን ጥናታዊ ስብሰባ ለመካፈል ዝግጅት ላይ እንገናኛለን። ስብሰባው የሚካሄደው ሳሳሪ ሳርዴኛ፣ ኢጣልያ ከሰኔ 3–5 2018 ድረስ ነው። በዚህ ስብሰባ ላይ የፓነል ውይይት የሚሳተፉ ተወካዮች ይኖሩናል።

## የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት

ከዚህ ቀደም ተዘጋጅቶ ከነበረው በራሪ በተሻለ መልኩ አስረጂ የሆነ፣ ጥረታችንን ሁሉ በደንብ የሚገልፅና ድርጅቱን በደንብ የሚያስተዋውቅ፣ በፒዲኤፍ ማውረድ የሚቻል እሱን የሚተካ ሰነድ አዘጋጅተን በማጠናቀቅ ላይ እንገኛለን። እንዳለቀም ከድረ-ገፁ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል።

ነሐሴ 2018 ሲመጣ አዚናራ ከሄድን ዓመት ይሞላናል። ለዚህም መታሰቢያ በሚሆን መልኩ ዓመት እስኪሞላን ድረስ **$20,000** ለመሰብሰብ እንድንረባረብ ባቀረብነው ጥሪ መሠረት እስከ አሁን የተሰበሰበውና ቃል የተገባው ድምር **$6,000** ነው።

ዋናው ዓላማችን አዚናራ ደሴት ላይ እዚያ ታስረው የነበሩ ወገኖቻችንን የምናስብበትና የምንዘክርበት ሚዩዚየም ማቆም ነው። አንዳንዶቹ ካምፖ ፋሮ መቃብር ቦታ ላይ ምልክት እንኳ በሌለው መቃብር አርፈዋል። ይህን ለማድረግ በተቻላችሁ መጠን ዓላማችንን እንደምትደግፉ ተስፋ አለን። እባካችሁ የገንዘብ ድጋፍም አድርጉልን። ማንኛውም የገንዘብ ድጋፍ ደረሰኝ የሚሰጥበትና ከግብር ነፃ የሚሆን ነው።

## አዲሱ ድረ-ገፃችን! FOM 2.0

አዲሱ FOM 2.0 ብለን የምንጠራው ድረ-ገፃችን መከፈቱን ስንገልፅላችሁ በደስታ ነው። ፒዬር ሀብቴ፣ ኤልፊና ይጥና እጅግ ደክመው ይህንን የተለየ ዲጂታል ጥራትና አቅም ያለውን ድረ-ገፅ በብዙ ወራት ልፋት እዚህ ስላደረሱልን በጣም እናመሰግናቸዋለን። ይህ አዲስ ድረ-ገፅ መዛግብት በውስጡ ለመያዝ ልዩ አቅም እንዲኖረው ሆኖ የተሠራ ነው። ወገኖቻችን ከእስር በፊት፣ ታስረው ሳለና ከተፈቱም በኋላ በአግባቡ ለመሰነድ ስለሚመቸን፣ ከዓላማችን ጋር እጅጉን የተጣጣመ ነው ብለን እናምናለን።

እባክዎ አዲሱን ድረ-ገፅ www.fromobliviontomemory.org ይጎብኙ። እግረ-መንገድዎን አዲስ የነደፍነውን የመገናኛ መንገድም ይፈትሹ!

---

የምናወጣቸው መረጃዎች የሚያስደስቱዎ ከሆኑ እባክዎ ድጋፍዎን ይስጡን፦

Donate

## ቋሚ ስብሰባዎች

- በሁለት ወር አንድ ግዜ፦ መሪ ኮሚቴ
- በየወሩ፦ የጥናት፣ መዛግብትና ሰነዳ ኮሚቴ፣ የፋይናንስ ኮሚቴና የግንኙነት ኮሚቴ
- በየዓመቱ፦ የቦርድ ስብሰባ

ቀጣይ ስብሰባዎችን ለመከታተል WhatsApp ላይ United የሚባለው ቡድን ላይ ያሉ መልዕክቶችን ይመልከቱ።

እኛን ለማግኘት፦ info@fromobliviontomemory.org

## አስተዋጽዖ አበርካቾቻችን

ይህ በየሦስት ወሩ የሚወጣ ዝግጅት ሲሆን የዛሬው የመጀመሪያው እትም ላይ ለተሳተፉትና ስማቸው ከዚህ በታች ለተጠቀሰው ምስጋናችን የላቀ ነው፦
ለምርምር፣ ለጽሑፍ እና ለዕርማት፦ ኅሕዓለም አሰፋ፣ እጅጋየሁ ደምሴ፣ ይጥና ፍርድይወቅ፣ ብርሃኔ ግርማቸው፣ መቅደስ መስፍን፣ ዋሲ ተስፋ፣ ሊዲያ ተስፋዬ፤ ያድዋ የወንድወሰን እና ዳግማዊ ይመር።
ለትርጉም፦ ደብሪቱ መርዕድ ካምፖሬያሊ፣ ጋብሪኤላ ጌርማንዲ፣ ኃይሌ ከበደ፣ ቆንጂት ሥዩም።
ለፎቶዎችና ምስሎች፦ ኤልፊ ጌታቸው ኑቬሎን፣ እያሱ ቤትዎስ፣ አሉላ ፓንክኸርስት።

© 2026 From Oblivion to Memory. All rights reserved.

FROM OBLIVION TO MEMORY
The FOM Newsletter
*Commemorating Ethiopian prisoners of the Italo-Ethiopian War*

VOL. 1 · NO. 1 JUNE / JULY 2026 fromobliviontomemory.org

← ወደ ዋናው ገጽ ተመለስ

# ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት፤ የትጋትና የጽናት ተምሳሌት

## ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት ከጻፉት ማስታወሻ የተወሰደ

…መርከቧ መልህቋን አነሳችና ወደ ሳርዴኛ አመራች። አስራ አምስትና ሀያ የሚሆኑ ፖሊሶች መሣርያ ይዘው ተከተሉን። ሦስትና አራት ሰዓት ያህል እንደተጓዝን ወደ የብሱ ስንቃረብ አንድ ጆንያ ሙሉ ሰንሰለት አምጥተው ፊታችን ዘረገፉ። ቀደም ብሎ ተወርቶ የነበረው የመታሰር ነገር እርግጥ ሆነ። ወዲያው ሁለት እጃችንን አስረው ሁለታችንን በረጅም ሰንሰለት አቆራኙን። ቺቪታቬኪያ ወደብ ወረድን። ዝግ ባለ የእስረኛ መኪና ወደ ባቡር ጣቢያ ወሰዱን። ሕዝቡ ተሰባስቦ እያጨበጨበ ደስታ ይገልጥ ነበር — ምርኮኞች ታስረው ሲያዩ ኩራት ይሰማቸዋል።


ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት በሮም አምባሳደር ሆነው

አንዳች በደል ሳንሠራ አወርደው ሰለሰሉን — አገራችንን በግፍ ስለቀሙን ሰላማዊነትን ስላሳየን እንዲህ አዋርደው እንደ ሌባ አደረጉን። ሮማ ቴርሚኒ ደርሰን ሌሎቹን ጠበቅን። ሁላችንም ከሰበሰብን ባቡር ተሳፍረን ተጉዝን። ምሳ ደረቅ ዳቦ ሰጡን — እጃችን ታስሮ በላን። ሌሊቱን ተጉዘን ሮሣኖ ወረድን፤ አውቶቡስ ሰፈረ — ጉዞ ቀጠልን።

አገሩ ተራራማ ገደል ነው — ካላብሪያ ከኢጣልያ ካርታ የእግር ጫማ ሚመስለው ጠርዝ ላይ ነን። ሲላ ሸንተረር አልፈን ሁለት ሰዓት ሲጓዙ ከገደል አፋፍ ላይ ባለ ሎንጎቡኮ ደረስን። ሕዝቡ በብዙ ሺህ እጅብ ብሎ ጠበቀን — ጥቁር ሰው ታይቶ ያልታወቀ ቦታ ነው። ሴቶቹም ልጆቹም ፈርተው ይደነቃሉ።

ቤት ውስጥ ሹማምንቱ ቆመው ጠበቁን። አገረ ገዥው (ፖዴስታው) "ወደ ኢጣልያ እንኳን ደህና መጣችሁ!…እዚህ ነፃ ናችሁ፤ እስራት የለባችሁም!" አለን። ሰንሰለቱ ወለቀ። ብዙዎቻችን እጃችን አብጦ ለማውለቅ ችግር ሆነ። ሴቶቹ ከፍርግርግ ዓይናቸው ሰደቃ ጠርጉ።


ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት

ወደ ማረፊያ ቤት ወሰዱን — ሁለት ፎቅ አፖርትመንት። ጓደኛ እየመረጥን ቦታ ያዝን። ሦስት ወጣቶች — አልቤርቶ፣ ካታልዶ፣ ሳልቫቶር — ተደልደሉልን። ሁሉም ቤት ባልኮን አለው፤ ጀርባ ሰፊ በረንዳ፤ ከላይ ትንሽ ቴራስ።

ሎንጎቡኮ የቀድሞ ስሟ ቴሜዚን ይባላል። ፈረንሳዮቹ ቆረቆሯት — ከስፓኞሎችና ቡርቦኖች ጋር ተወርረው አልቀዋል። ሦስት ሩብ ዙሪያ ገደል ነው፤ ቀሪ ፊት ጫካ። ሰማይና ተራራ ብቻ ይታያሉ — ሎንጎቡኮ ማለት ረዘም ያለ ጉድጓድ ተብሎ ይተረጎማል።

ቀስ ብዬ ሰጋሁ — ይህን ጥልቅ ቦታ ያመጡን ቶሎ አይፈቱን። ወደ ካራቢኔዬሮች ጽሕፈት ቤት ሄድን። አንድ ባንድ ቀርበን ስም፣ ዕድሜ፣ ጎሳ፣ ሥራ፣ ሃይማኖታችን ሁሉ ተጠይቀን ተመዘገብን።

2026 From Oblivion to Memory. All rights reserved.

FROM OBLIVION TO MEMORY

The FOM Newsletter

*Commemorating Ethiopian prisoners of the Italo-Ethiopian War*

VOL. 1 · NO. 1 JUNE / JULY 2026 fromobliviontomemory.org

← ወደ ዋናው ገጽ ተመለስ

# ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ፤ በአዚናራ የብርታት ተምሳሌት

አርበኛ፣ መምህርት፣ የሕዝብ ተወካይ፣ ደራሲ እና የሴቶች መብት ተሟጋች



ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ

በኢትዮጵያ ታሪክ ቀደምት ከሚባሉት ዘርፈ ብዙ ባለሙያ የሕዝባቸው አገልጋይ የነበሩት ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ አርበኛ፣ መምህርት፣ በፓርላማ የሕዝብ ተወካይ፣ የሴቶች መብት ተሟጋች ነበሩ። ወይዘሮ ስንዱ በ1908ዓ.ም. ተወልደው፣ በአውሮፓ ለመማር ዕድል ካገኙት ጥቂት ኢትዮጵያውያን ሴቶች መካከል አንዷ ሲሆኑ፣ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ ያላቸውን የታሪክ እውቀትና የሥነ ጽሑፍ ፍቅር በመጠቀም አገራቸውን በፅናት ሲያገለግሉ ኖረዋል።

ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የጥቁር አንበሳን የጦር ድርጅት መሥራች አባል ሲሆኑ፣ የመጀመሪያዋ እንስት አባል ሆነው አገልግለዋል። በኋላም ጫናው ሲበዛ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ወይዘሮ ስንዱን ከሃገር እንዲወጡ ሊያሳምኗቸው ቢሞክሩም፣ ወይዘሮ ስንዱ አሻፈረኝ በማለት ጥቁር አንበሳ ሲመሠረት አባላቱ የገቡት ቃለ መሓላ አገር ጥሎ መውጣት እስከ ሞት ድረስ ቅጣት እንደሚያስከትልና እርሳቸውም እዚያው ለመቆየት እንደወሰኑ ገልፀውላቸው፣ እንደውም ራስ እምሩ ቢፈቅዱና ድጋፍ ቢሰጧቸው የቀይ መስቀል ክንፍ መሥርተው ለጦሩ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ እንደሆኑ ባሳመኗቸው መሠረት እዚያው ቆይተው ቀይ መስቀልን መሥርተው አገልግለዋል።

ግራዚያኒን ለመግደል የተደረገው ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ሁለት ዕድሜአቸው ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላ ደበበና ኃይሉ የተባሉ የወንድማቸው ልጆች፣ ታናሽ ወንድማቸው መሸሻና ሌሎችም ብዙ የጥቁር አንበሳ አባላት በተገኙበት ተገድለዋል። ወይዘሮ ስንዱና በርካታ የቤተሰባቸው አባላት ታፍሰው ወደአዚናራ ተወሰዱ። በዚያ የነበረው የኑሮው ሁኔታ በጣም ከባድ፣ ብቸኝነቱና ከሰው መነጠሉም እጅግ አስከፊ ቢሆንም ወይዘሮ ስንዱ በብርታታቸው ተወጥተውታል።

በሚገባቸው ቋንቋ ሁሉ መጻሕፍት ማግኘት ባለመቻላቸው ወይዘሮ ስንዱ በራሳቸው ትጋት ጣልያንኛ መናገርና ማንበብ ተለማምደው፣ ያጋጠማቸውን እንቅፋት ወደ ዕድል የለወጡ ሰው ናቸው። አብረዋቸው ለታሰሩ ሰዎች መብት በመቆም፣ በተለየ ሴቶቹ እስረኞች አያያዛቸው እንዲሻሻል ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። እኅት ወንድሞቻቸውንም በመጠበቅ በተለይ እኅታቸው ደስታ ገብሩን ጠፍተው አዚናራ ደሴት ወደሚገኝ ገዳም እንዳይገቡ ታድገዋቸዋል።

አዚናራ ደሴት ላይ በነበሩበት ጊዜ ወይዘሮ ስንዱ አብረዋቸው ከታሰሩ ሰዎች ጋር የዕድሜ ልክ ወዳጅነት መሥርተው ለአገራቸው ያላቸውን ተዓማኒነትና ለነፃነት ያላቸውን ጥማት ሲጋሩ ኖረዋል። የጥቁር አንበሳ መሥራች አባልነት ተሞክሮአቸውና የአዚናራ እስረኝነታቸውን አቀናጅተው "የልቤ መፅሐፍ" የተሰኘ የጣልያን ወረራና የኢትዮጵያውያንን አርበኝነትን የሚዘግብ ታሪካዊ ድራማ ደርሰዋል።

ጥቁር አንበሳ ውስጥና አዚናራ ላይ ያሳለፉት ጊዜ በኋላ አገርን ለማገልገል ሰፊ መሠረት ጥሎላቸዋል። ወይዘሮ ስንዱ ከነበሯቸው እጅግ ብዙ ኃላፊነቶች አንዳንዱን ለማንሣት ያህል፣ የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ዳይሬክተር፣ የፓርላማ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የቀይ

መስቀል ኃላፊ፣ የኢትዮጵያ ሴቶች በጎ አድራጎት ማኅበር አመራር፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች ማሕበር አመራር በመሆን አገልግለዋል።

በኋላም ወይዘሮ ስንዱ በ1940ዎቹ ውስጥ ሻለቃ ለማ አሰፋን (በኋላ አምባሳደር) አግብተው የአራት ልጆች እናት ሲሆኑ፣ አገራቸውን እና ሕዝባቸውን ማገልገላቸውን ቀጥለዋል። በ2001 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም ድካም በ94 ዓመት ዕድሜአቸው እስካረፉበት ጊዜ ድረስና ከዚያም በኋላ ስማቸው የትጋት፣ የፅናትና የሕዝብ አገልግሎት ተምሳሌት ሆኖ ይኖራል።

ወይዘሮ ስንዱ አዚናራ በእስረኝነት የነበሩበት ዘመን ያጋጠማቸውን ተግዳሮት የተወጡበት መንገድ ሁሉ የሰው ልጅ ፈተናን ተቋቁሞ የራሱንም ሆነ የወገኑን ሕይወት ለማስቀጠል ላለው አቅም ምስክርነት የሚቆም ነበር። እሳቸው ራሳቸው እስረኛ ሆነው ሳለ ቤተሰባቸውን ጨምሮ ሌሎች እስረኞችን ለመታደግ የነበራቸው አቅም ከነፃነት በኋላ አገራቸውን በብቃት ለማገልገል እንደረዳቸው ጥርጥር የለውም።

2026 From Oblivion to Memory. All rights reserved.

FROM OBLIVION TO MEMORY
The FOM Newsletter
*Commemorating Ethiopian prisoners of the Italo-Ethiopian War*
VOL. 1 · NO. 1 JUNE / JULY 2026 fromobliviontomemory.org

← ወደ ዋናው ገጽ ተመለስ

# ጥቁር አንበሳ፤ የተደራጀ የፀረ ጭቆና ትግል ተምሳሌት

ፀረ ፋሽስት ትግልን ስለ ጀመሩ ኢትዮጵያውያን አጭር ታሪክ


የጥቁር አንበሳ አባላት

## መግቢያ

ጥቁር አንበሳ የተባለው ቡድን የተቋቋመው ምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ በ1928 ዓ.ም. (ዐፄ ኃይለሥላሴ ተሰድደው ፋሽስት ጠላት ዐዲስ አበባን እንደያዘና የነፃነት ትግል ስልቱ ሽምቅ ውጊያ መሆን እንደጀመረ) ነበር። በዚያን ጊዜ ፀረ ፋሽስት ንቅናቄ አውሮፓ ውስጥ (ኢጣልያ ጭምር)ገና አልተጀመረም ነበር።

የጥቁር አንበሳ ታሪክ ተገቢውን ትኩረት አላገኘም እንጂ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ኩራት ያቀፈ በቅኝ አገዛዝ ላይ የተደረገ የተደራጀ ትግል ነበር። አባላቱም ዘመናዊ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ያላቸው ነበሩ። ብዙዎቹም ዘመናዊ ወታደራዊ ስልቶችን የተማሩ ነበሩ። ጥቁርአንበሳ ኅልውናው ዐጭር፥ የአባላቱ ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም፣ የመጀመሪያው ፀረ ፋሽስታዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴና በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአፍሪካ የመጀመሪያው የተደራጀ ፀረ ጭቆና ትግል ነው ሊባል ይችላል። ጥቁር አንበሳ የተደራጀ የፀረ ጭቆና ትግል ተምሳሌት እና ሕያው ምስክር ነበር። ታሪኩ አስከፊውን የፋሽስት ግፍ እና ጭካኔ በማጋለጥ ስሜትን የሚስብ ነው።

## የጥቁር አንበሳ አባላት እነማን ነበሩ?


ሳምሶን እና ቢኒያም ወርቅነህ

የጥቁር አንበሳ አባላት የመጡት መጠነኛ መደራረብ ከነበራቸው ከሚከተሉት ሦስት ምድቦች ነበር፦

1. ወታደራዊ ካድሬዎች – ክፍሌ ነሲቡ (የአፈንጉሥ ነሲቡ ዛማኤል ልጅ)፣ ነጋ ኃይሌሥላሴ (በኋላ ጄኔራል) እና ሌሎች የሆለታ ወታደራዊ አካዳሚ ምሩቆች
2. ምሁራን – ከታላቋ ብሪታንያ የተላኩት ፊቃደ ሥላሴ ኀሩይ (የንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ)፥ እንዲሁም ሳምሶን ወርቅነህ እና ቢኒያም ወርቅነህ (የሐኪም ወርቅነህ እሸቴ ልጆች)፥ ተቃውሞውን ለመቀላቀል ከውጭ የተመለሱት ወርቅነህ፥ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ እና ሌሎችም
3. የመኳንንት ቤተሰብ አባላት – ደጃዝማች ወሰን፣ መሸሻ ገብሩ እና ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ (የከንቲባ ገብሩ ልጆች)፥ ይልማ ዴሬሳ፥ ራስ እምሩ

ቡድኑ የውትድርና ሥልጠና ያገኙ ምሩቆችን እንዲሁም ውጭ ሀገር የተማሩ ልሂቃንን ያቀፈ ነበር። የጥቁር አንበሳ መሪ ዓለምወርቅ በየነ ብሪታንያ ውስጥ የተማሩ፥ ችሎታ እና ሥርዓትን አጣምረው የያዙ የእንስሳት ሐኪም ነበሩ።



ዓለምወርቅ በየነ

## መሪ መርሆዎች

- ወታደራዊ ኃይሉ የሚመራው በፖለቲካዊ ዐቋም መሠረት ነው።
- ለኢትዮጵያ እና ለንጉሡ ነገሥቷ ፍጹም ታማኝ።
- ለጠላት እጅ መስጠት አይፈቀድም — ሞት ይመረጣል።
- ማፈግፈግም መሰደድም የለም።
- ሲቪሎችን መጠበቅ ብሔራዊ ግዴታ ነው።
- የምርኮኞች አያያዝ ሰብዓዊ ሊሆን ይገባል።
- ማጭበርበር አይፈቀድም።
- መሪዎች የተማሩ፥ ውሳኔዎች ስልታዊ ሊሆኑ ይገባል።
- እንቅፋቶች ቢኖሩም ትግሉን መቀጠል ይገባል።
- ብሔራዊ አንድነት ከሁሉ ይቀድማል።

## የጥቁር አንበሳ የትግል ሚና

ዐዲስ አበባ ስትወድቅ ወታደሮቹ ጫካ ገቡ — ተበታትነው። ጥቁር አንበሳ ዘመናዊ ድርጅቱን ሰንቆ ተቃውሞ ለማስተባበር ምዕራብ ወጣ። ራስ እምሩን ደግፎ የአንድነት ራዕይ አራምዷል — ዐጭር ጎልውናው እንኳን ዘላቂ ምልክት ትቷል።

## የነቀምት ክሥተት

ዐዲስ አበባ ከወደቀች በኋላ ብዙ የጥቁር አንበሳ አባላት ነቀምት ሄዱ። ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ኩምሳ ኢጣልያን ሊያናድድ ነው ብሎ ስላሳሳባቸው ጥቁር አንበሳ ቆዩ። ሆኖም የኢጣልያ አየር ኃይል ቡድን ሲቀርብ ጥቁር አንበሳ ጥቃት ፈጸሙ — ሦስት አውሮፕላኖች ወደሙ፣ ልዑካኑ ሁሉ ተገደሉ። ኢጣልያ አጸፋ ሰጠ — ነቀምቴን ደበደቡ፣ ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን ጥቃቱ ተሳታፊ አደረጉ — ብዙም ሳይቆዩ ዐረፉ።



ደጃዝማች ሀብተ ማርያም

ራስ እምሩ በጥር 1929 ዓ.ም. እጃቸውን ሲሰጡ ሲያልቅ የጥቁር አንበሳ ትግልም ፍጻሜ ሆነ። ከተያዙት ሰባት አባላት ይልማ ዴሬሳ እና ሐዲስ ዓለማየሁ ወደ ኢጣልያ ሄደው ሕይወታቸው ዳነ። ሌሎቹ — ቢኒያም ወርቅነህ፣ ሳምሶን ወርቅነህ፣ ፈቃደ ሥላሴ ኅሩይ፣ መሸሻ ገብሩ — ተገደሉ።

## ጥቁር አንበሳ እና አርበኞች

ጥቁር አንበሳ ለኢትዮጵያ ነፃነት ብቸኛ ድርጅት አልነበረም። ብዙ አርበኞች ኢትዮጵያ ነፃ እስከወጣችበት 1933 ዓ.ም. ድረስ ታግለዋል። ባህላዊ አርበኞችና ዘመናዊ ጥቁር አንበሳ አንዳንድ ጊዜ ይተባበሩ አንዳንድ ጊዜ ይጋጩ ነበሩ — ሁለቱም ለሃገር ናፍቆት ታጥቀዋል።

## መዝጊያ

ዛሬ ጥቁር አንበሳ የሚታሰበው ያልተሳካ ሙከራ ሆኖ ብቻ አይደለም። ብዙ ሳይቆይ ቢቀጨጭም፣ ሥርዓት፣ ድርጅት፣ ብሔራዊ ራዕይ አቀናጅቶ ነበር። አባላቱ ተዋጊዎች ብቻ አልነበሩም — ክብር ሊኖር ተቃውሞ ሊደራጅ፣ ሕዝብ በፍራቻ ሳይሆን በመርህ አንድ ሊሆን ይቻላል ብለው ያምኑ ነበር። ያ ዕምነት ዛሬም ተጋባ ሆኖ ይኖራል።

2026 From Oblivion to Memory. All rights reserved.